# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት





## በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓት አተገባበር፣ክትትልና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት









ታህሣስ/2005 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ


ክፍል አንድ ...1

መግቢያ ...1

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አመሰራረት...1

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር ...2

የባለስልጣኑ ዓላማ ...2

የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ...2

የፌዴራል አካባቢ ጥባቃ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል ...4

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የፋይናንስ ምንጭ...5

የአካባቢ እንክበብካቤ ስርዓትን በዘላቂነት የማስፈን የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description) ...6

የኦዲቱ አላማ...8

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ...8

የኦዲቱ አከባቢ ...9

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ...9

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ...10

ክፍል ሁለት ...11

የኦዲት ግኝቶች...11

I. በባለስልጣኑ በተዘገቡ ዘገባዎች /The state of the environment reports/ መሰረት የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓትን ለማስፈን የወጡ የአካባቢ አዋጆች፣ደንቦች፣ደረጃዎች እና መመሪያዎች ተፈፃሚነትን እና ውጤታማነትን ለመገምገም ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ...11

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት በማድረግ ዓመታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጅና በዕቅድ አፈፃፀሙ ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ፤ ...11

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ እያዘጋጀ ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፣...12

ባለስልጣኑ አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ ማዘጋጀቱን እና በስራ ላይ መዋሉን መከታተሉን በተመለከተ፣ ...13

የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት ፣ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚረዱ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎችን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት መላኩን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፣ ...15

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፣...18

II. ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ...20

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣...20

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና የዘርፍ መ/ቤቶች የክትትልና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የሚልኩለት መሆኑን በተመለከተ፣ ...22

III. የአካባቢ አሃድ/Enivronmental unit/ በዘርፍ መ/ቤቶች መቋቋሙን እንዲሁም በወጡ የአካባቢ ስርዓት አተገባበር ላይ ለኢንዱስትሪዎችና ለባለድርሻ አካላት የሚደረገው ክትትልና ግምገማ ብቃት ባለው መልኩ መደረጉን በተመለከተ፡ ..................23

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አሃድን የሚከታተል ክፍል ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች እንዲያቋቁሙ ማድረጉን በተመለከተ፣ ....................23

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ግምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ማሳወቁን በተመለከተ፣ ....................25

ባለስልጣን መ/ቤቱ ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፣ ....................26

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸቱን በተመለከተ፣ ........29

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፋብሪካዎች የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፣ ....................31

ክፍል ሦስት ....................35

የመደምደሚያ ሃሳቦች ....................35

ክፍል አራት ....................38

የማሻሻያ ሃሳቦች ....................38

አባሪ 1 ....................I

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ....................I

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

## የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አመሰራረት

1. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአገሪቷን የተፈጥሮ ሀብት ዘላቂነት ባለው መልኩ በጥቅም ላይ ለማዋል እና በመጥፋት ላይ ያሉትም ሊያገግሙ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር እዲያስችል በ1987 ዓ.ም በሚኒስተሮች ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 9/1987 ዓ.ም ተቋቁሟል፡፡

2. በአገሪቷ ያለውን የአካባቢ ሁኔታን በመቃኘት ሀገሪቱ በአካባቢ ሀብቶች የታደለች በመሆኗ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት ለመንከባከብና በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል በአካባቢ እንክብካቤ ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ልማትን ለማራመድ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደረጃጀቱን የማስተካከል እርምጃ በመውሰድ በአዋጅ ቁጥር 295/1995 በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

3. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሰረት የአካባቢ ጥበቃ ሥርዓቶች በመዘርጋት የአካባቢ እንክብካቤን በዘላቂነት የማስፈን፣ የመከታተል እና የመቆጣጠር ሥራ ለመስራት የሀገሪቱን የአካባቢ ፖሊሲ፣የእንክብካቤ ስልቶች እና የአካባቢ ኮንቬንሽኖች ፀድቀዋል፡፡ በተጨማሪም የብክለት ቁጥጥር አዋጅ 300/1995፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ 299/1995፣ የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ፣የከተማ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አዋጅ 513/1999 እንዲሁም የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ 159/2001 ወጥተዋል፡፡ የአካባቢ ደረጃዎችና መመሪያዎችም ተዘጋጅተዋል፡፡

4. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአካባቢያዊ ሃብቶች በዘላቂነትና በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓትን በመዘርጋት የአካባቢ ሁኔታና ጥናት ዘገባ፣የአካባቢ ስልታዊ ዕቅድ፣የአካባቢ ህግን እና የአካባቢ ደረጃዎችን የማዘጋጀት፣ለተግባሪዎችና አስተግባሪዎች እገዛ የማድረግ፣ አስተግባሪዎች የወሰዱትን የሕግ የማስከበር እርምጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የሥርዓቱን ውጤታማነት የመገምገም ስራን ይሰራል፡፡

# የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር

## የባለስልጣኑ ዓላማ

5. የባለስልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሰውን በጎ ሁኔታ እና የአካባቢን ደኅንነት በዘላቂነት ሊያራምዱ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ሥልቶችን፣ ሕጎችንና ደረጃዎችን ማዘጋጀት እና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር በግንባር ቀደምትነት መምራት ነው።

## የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

6. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 295/1995 ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-

   - በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ የአካባቢ ደኅንነት ዓላማዎች በአካባቢ ፖሊሲው የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፣
   - አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች፣ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላትና ከሕዝብ ጋር በመመካከር የአካባቢ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችንና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፣ ያሻሽላል ወይም እንዲዘጋጁ ያስደርጋል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
   - አካባቢን ለመጠበቅና የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ፣ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣ እንደአስፈላጊነቱ የአቅም ግንባታዎች ይሰጣል፣
   - በመንግስትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ህጎችና መርሐ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ለማካሔድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣
   - የሥራ ፍቃድ የመሥጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ሥልጣን የፌዴራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ ይገመግማል፣ ለፍቃድ ሰጭው አካል ውሳኔውን ያሳውቃል፣ እንደተገቢነቱም የትግበራውን ይሁንታ ሲሰጥ በተመለከቱ ግዴታዎች መሠረት ፕሮጀክቶቹ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣

- አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመሆን በረሃማነትን ለመከላከል፣ የድርቅን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሄዳል፣ መፍትሄዎችን ያዘጋጃል፣ ለአተገባበራቸውም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣
- አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ ደረጃዎችን ይወስናል፣ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣
- አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር በዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ እንደተገቢነቱም ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፣ ወይም እንዲቀርብ ያስደርጋል፣
- አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ስልቶች፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጅ ሃሳብ ያመነጫል፣አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፣ሲፈቅዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
- አደገኛ ንጥረነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን፣ እንዲሁም ሕያዋንን በዘለመል ምሕንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደኅንነት ፖሊሲዎችና ሕጎችን አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣ሲፈቅዱም በሥራ ላይ መዋላቸው ያረጋግጣል፣
- በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሀግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓትን አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ እንደሁኔታውም በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፣
- ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምንና ልምድን፣የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ሃሳብ ያቀርባል፣
- አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣አደረጃጀትንና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣
- የአካባቢ ጥበቃ ምርምሮችን ያስተባብራል፣ያበረታታል፣እንደአስፈላጊነቱም ራሱ ያካሄዳል፣

- አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በፌዴራሉ ሥልጣን ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፣ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፣ናሙናዎችን ይወስዳል፣
- የአገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግሥትም ለሕዝብም እንዲደርስ ያደርጋል፣
- መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፣ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፣
- የአካባቢ ጥበቃ የድርጊት ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያበረታታል ወይም ያግዛል፣ለድርጊት ዕቅዶቹና ፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውሉ እገዛዎችን ያፋልጋል፣
- የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣
- የአካባቢ አያያዝና ጥበቃን ተቀዳሚ ዓላማው በማድረግ ለሚሰራ ማንኛውንም ድርጅት ወይም ግለሰብ ምክር እንዲሁም የሚቻል ሲሆንና የአካባቢ ምክር ቤት ሲሰማማበት የፋይናንስ እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣
- የአካባቢ አያያዝ እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣
- አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች በዚህ ዓዋጅና በሌሎች አካባቢ ጥበቃን በሚመለክቱ ሕጎች የተጣለባቸውን ኃላፊነቶች በሚወጡበት ሁኔታ ምክር ይሰጣል፣አዳስፈላጊነቱም እርምት ሊወስድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ለመንግሥት ያቀርባል፣
- በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ ሁኔታዎችን ለማቋቋም ስለሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎች መንግሥትን ያማክራል፣

## የፌዴራል አካባቢ ጥባቃ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

7. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሆኖ በአንድ ዋና ዳይሬክተር፣ በአንድ ም/ዋና ዳይሬክተር፣ በ15 ዋና የስራ ሂደት እና ድጋፍ ሰጭ ዳይሬክቶሬቶችና በ2 ጽ/ቤቶች ተዋቅሯል:: የዋናው የስራ ሂደት አራት ፕሮግራሞች ያሉትና በነዚህም ስር 8 ዳይሬክቶሬቶችን ይዟል:: ለባለስልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላው 223 የሰው ዓይል እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለዋና የስራ ሂደቶች የተፈቀደው 119

የሰው ሀይል ነው፡፡ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ በባለስልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል 141 መሆኑን ከሰው ሀብትና ንብረት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከተሰበሰበ መረጃ ለማውቅ ተችሏል፡፡

## የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የፋይናንስ ምንጭ

8. የአካባቢጥበቃ ባለስልጣን ስራውን የሚያከናውነው በመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ2002፣በ2003 እና 2004 በጀት ዓመታት እንደየቅደምተከተሉ ከመንግስት የተመደበለት መደበኛ በጀት ብር 5,554,700.፤ ብር 5,867,861እና ብር 8,756,730 ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2002 በጀት ዓመት ብር 4,325,349.13፤ በ 2003 በጀት ዓመት ብር 5,192,230.56 እንዲሁም በ 2004 በጀት ዓመት ብር 6,395,483.44 ስራ ላይ አውሏል፡፡

# የአካባቢ እንክበብካቤ ስርዓትን በዘላቂነት የማስፈን የስራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

9. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ እንክበብካቤ ስርዓትን በዘላቂነት የማስፈን የስራ ሂደት ያለው ሲሆን ይህም የስራ ሂደት ዘላቂ የአካባቢ አያያዝና በአካባቢ ሃብቶች አጠቃቀም ሥርዓትን ለማስፈን ቅድሚያ የወቅቱን የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ለማወቅ የሚያስችል ሥራ በአከባቢ ሁኔታ ለውጥ ጥናትና ዘገባ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም የአካባቢ አመላካቾች ላይ መሠረት በማድረግ መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀት መረጃው በመረጃ ቋት ይያዛል፡፡ በዋናነት ከመረጃ ቋቱ በሚገኘ መረጃና ሌሎች የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም እንዲሁም የተቀናጀ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ጥናት ዘዴን በመጠቀም የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባም ይዘጋጃል፡፡
10. በተቀናጀ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ጥናት ውጤት ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫን መሠረት በማድረግ በወቅቱ የታዩትን ዋና ዋና የአካባቢ ችግሮችን በመፍታት ወደተሻለ የአካባቢ ሁኔታ ለመድረስ የሚያስችሉ ዋና ዋና ግቦች፣ ሥልቶችና ቁልፍ ተግባራትን ያካተተ የረጅምና የአጭር ጊዜ ስልትና ዕቅድ ይዘጋጃል፡፡ በስልትና ዕቅድ ዝግጅቱ ሆነ በትግበራው ባለድርሻዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡
11. በመቀጠልም ለዘላቂ የአካባቢ አያያዝና የአካባቢ ሃብቶች አጠቃቀም ስልትና ዕቅድን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊው የህግና የቴክኒክ ደረጃዎች ሥርዓት በስርዓት ዝግጅት እና በአካባቢ ደረጃ ዳይሬክቶሬቶች ይዘጋጃል፡፡ የዋና ሥራ ሂደቱ ትኩረት ሥርዓቱ በሚወስነው መሰረት ዘላቂ የአካባቢ አያያዝና በአካባቢ ሃብቶች አጠቃቀም ሥርዓትን ለሚተገብሩና ለሚያስተገብሩ ባለድርሻ አካላት ሥልጠና ለመስጠትና ክህሎት ለማዳበር፣ግንዛቤ የማሳደግ ስራ በትምህርትና ግንዛቤ ዳይሬክቶሬት ይሰራል፡፡ የአካባቢ ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅ እና የፋይናንስ ፍላጎት በሚሟላት የአከባቢ እንክብካቤ ስርዓት ተግባሪና አስተግባሪ ባለድርሻዎችን የማገዝ ሥራ በቴክኖሎጅ ሽግግር እና በፋይናንስ ዳይሬክቶሬቶች ይከናወናል፡፡
12. የአካባቢ አያያዝና የአካባቢ ሃብቶች አጠቃቀም ሥርዓት ተከባሪነትን ለማረጋገጥ በተግባሪዎችና በአስተግባሪዎች ላይ የቁጥጥር፣ የክትትል እና የግምገማ ሥራ በክትትልና ግምገማ እና በአካባቢ አሀድ ዳይሬክቶሬቶች ይካሄዳል፡፡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከማስፈፀም አኳያ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በመቀበል የሚመለከታቸው አስተግባሪዎችን ሃሣብ በማካተት ውሣኔ የመስጠት ሥራ ይከናወናል፡፡

13. በአጠቃላይ የሥራ ሂደቱ ትግበራ ከተቀመጡት ዓመታዊም ሆነ የሥልታዊ ዕቅዱ ዘመን ግቦች አንፃር ያመጣውን ለውጥ የተመለከተ ግምገማ እንዲካሄድ የሚደረግ ሲሆን የግምገማው ውጤት ለቀጣይ የስራቱ ዑደት ዙር መነሻ ለሆነው ለአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ጥናትና ዘገባ ዝግጅት ግብዐት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

14.የኦዲቱ ዓላማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ሥርዓትን ማስፈንና የክትትል ስራ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መልኩ በአግባቡ መከናወኑን እና አፈፃፀሙ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች /EGAS/ እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 እስከ 2004 በጀት ዓመታትን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሲሆን የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የወጡ ፖሊሲ፣አዋጆች፣ ደንቦች፣ ደረጃዎች እና መመሪያዎችን የሚተገብሩ ስምንት ዓይነት የኢንዱስትሪ ዘርፎች፣ እና ከሚያስተገብሩ 2 መስተዳድሮችና 9 የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ውስጥ በናሙና መርጦ በማየት የተለያዩ መረጃዎችን በመክለስና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት/የዘርፍ መ/ቤቶች/ የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና መጠይቆችን በመላክ እንዲሁም አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡ በናሙና የተመረጡ ክልሎች የተመረጡበት ምክንያት ባላቸው የፋብሪካ ብዛት እና ዓይነት ሲሆን ከተለያዩ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በአካባቢ ላይ በአሁን ወቅት የአካባቢ ተፅዕኖ በማስከተል ይገኛሉ ብለው ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት ከላኩት መረጃ እና በተለያዩ ሚዲያዎች/ሬዲዮ.ቲቭ/ ላይ አካባቢን ከመበከል አንፃር የሚጠቀሱ የኢንዱስትሪ ዓይነቶች እና በማህበረሰቡ ከሚቀርበው አቤቱታ አንፃር የቆዳ፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የኬሚካል፣ የምግብና የመጠጥ፣ የሲምንቶ፣ የስኳር እንዲሁም የብረታብረትና የማተሚያ ቤት ኢንዱስትሪዎች ተመርጧል::

16.በዚህም መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ 9 ነባርና 4 አዲስ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልላዊ መንግስት የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ 4 ነባርና 1 አዲስ በድሬደዋ ከተማ አስተዳድር ለድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ 4 ነባር፣ በሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣ 2 ነባር፣ በኦሮሚያ ክልል ለገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮ ፣9 ነባርና 5 አዲስ፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

ባለስልጣን 7 ነባርና 1 አዲስ ፋብሪካዎች በድምሩ ለ46 ፋብሪካዎች(15 የቆዳ፣8 የጨርቃ ጨርቅ፣ 8 የኬሚካል፣ 8 የምግብና የመጠጥ፣ 3 የሲምንቶ፣ 2 የብረታ ብረት፣ 1 የስኳር እና 1 የማተሚያ ቤት)፣ ለስድስት የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና ለ3 የዘርፍ መ/ቤቶች/ማዕድን ሚ/ር፣ ለግብርና ሚኒስቴር እና የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር/የኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት በአካባቢ እንክብካቤ ስርዓት አተገባበር እና ክትትል ጋር የተያያዙ የተለያዩ ማስረጃዎች /ዶክሜንቶች/ በመከለስ፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና የስርዓቱን አተገባበር በአካል ተገኝቶ በማየት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እንዲሁም ለ10 የዘርፍ መ/ቤቶች/ ለመንገዶች ባለስልጣን፣ ለኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን፣ ለካርታ ስራዎች ድርጅት፣ ለመድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለንግድ ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ቴሌ ኮሚኒኬሽን፣ ለጨርቃ ጨርቅ እና ቆዳ ኢንስቲትውት መጠይቆችን (Survey questionnaires) በመላክ ከስድስት የዘርፍ መ/ቤቶች መረጃዎች በመሰብሰብ ኦዲቱን ተከናውኗል፡፡

## የኦዲቱ አከባቢ

17.ለክዋኔ ኦዲት የተመረጠው የኦዲት አከባቢ የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓት አተገባበር፣ ክትትል እና ቅንጅታዊ አሰራር በአዋጁ መሰረት በአግባቡ መፈፀሙንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

18.ከላይ በተመለከተው የኦዲት አከባቢ ስር ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡

እነርሱም፡-

1. በባለስልጣኑ በተዘገቡ ዘገባዎች መሰረት የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓትን ለማስፈን የወጡ የአካባቢ አዋጆች፣ደንቦች፣ደረጃዎች እና መመሪያዎች ተፈፃሚነትን እና ውጤታማነትን ለመገምገም ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

2. ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. የአካባቢ አሃድ/Enivronmental unit/በዘርፍ መ/ቤቶች መቋቋሙን እንዲሁም በወጡ የአካባቢ ስርዓት አተገባበር ላይ ለኢንዱስትሪዎችና ለባለድርሻ አካላት የሚደረገው ክትትልና ግምገማ ብቃት ባለው መልኩ መደረጉን መገምገም፡

ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

19. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት በአከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የወጡ አዋጆች እና ደንቦች፣ በአከባቢ ጥበቃ የሚገኙ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ዶክሜንቶች (BPR documents) ፣ የእስትራቴጅክ ዕቅዶች ፣ የውል ስምምነቶች እና ቃለ-መጠይቆች ናቸው፡፡ በተዘጋጁትም የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር **በአባሪ 1**ተያይዘዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### I. በባለስልጣኑ በተዘገቡ ዘገባዎች /The state of the environment reports/ መሰረት የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓትን ለማስፈን የወጡ የአካባቢ አዋጆች፣ደንቦች፣ደረጃዎች እና መመሪያዎች ተፈፃሚነትን እና ውጤታማነትን ለመገምገም ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

***የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት በማድረግ ዓመታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጅና በዕቅድ አፈፃፀሙ ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ የሚወስድ መሆኑን በተመለከተ፤***

20. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በስትራቴጂክ ዕቅድ ያቀደውን ተግባራት በዓመታዊ ዕቅድ ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም በየዓመቱ በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት መሰረት ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
21. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት ምንጮች ጉዳት ላይ ሊወድቁ የሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚለይ ዘገባ እና በዘርፍ መ/ቤቶች የሚገኙ ሰነዶች በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ሊከሰቱ ከሚችሉ ጉዳቶች የሚያጣጥም የአሰራር ማንዋል ለማዘጋጀት፤ እንዲሁም ከአጋሮች ጋር በመስራት የአካባቢ ትምህርት በመደበኛ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተት የማድረግ ስራ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ቢያካትትም ይህንን ተግባር በዓመታዊ ዕቅዱ ውስጥ በማካተት ተግባራዊ አለማድረጉ ታውቋል፡፡
22. ከዚህም በተጨማሪ ባለስልጣኑ ከ2002-2004 ዓ.ም ባዘጋጃቸው ዓመታዊ ዕቅዶች መሰረት በየዓመቱ መጨረሻ ላልተከናወኑ ተግባራት ይኸም የአካባቢ መረጃ ስርዓት ዝርጋታ፣ በ8 የኢንዱስትሪ ዘርፎች የአፈፃፀም መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፣ የአካባቢ ብክለት መመሪያ፣ የረግረጋማ መሬቶች አያያዝ ህግ፣ የአካባቢ ደንነት ማረጋገጫ መስፈርት በመንግስትና በግል ድርጅቶች የአሰራር መመሪያ፣ የምርቶች የአዛላቂነት ደረጃዎች ህግ እና በአበባና ሆርቲካልቸር ዘርፎች ላይ መዘጋጀት የሚገባቸውን መመሪያዎች አዘጋጅቶ የማስፀደቅ ስራዎች ዙሪያ የታዩ ክፍተቶች በዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ቢታይም እነዚህን ክፍተቶች ለማስተካከል የሚያስችል በተሟላ መልኩ የእርምት እርምጃ አለመውሰዱ ተረጋግጧል፡፡
23. ስለሁኔታው የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለስልጣን መ/ቤቱ በሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት ምክንያት ጉዳት ላይ ሊወዲቁ የሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሚለይ ዘገባ

እና በዘርፍ መ/ቤቶች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊከሰቱ ከሚችሉ ጉዳቶች የማጣጣሚያ የአሰራር ማንዋል እንዳዘጋጀና የተዘጋጀውንም ሰነድ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዳስተቸ እንዲሁም በዕቅድ አፈፃፀሙ የታዩ ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚያስችል የእርምት እርምጃ አለመውሰዱን በተመለከተ የህግ ዝግጅቶችን በረቂቅ ደረጃ ያዘጋጀ መሆኑን እና ህጎቹን ለማስፀደቅ ባለፈው የበጀት ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ሳይፀድቅ መቅረቱን የገለፁ ቢሆንም እስከ ኦዲቱ መጨረሻ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ የተተቸው እና የተዘጋጁትን ረቂቅ ህጎችና የአሰራር ማንዋሎች ማስረጃ ለማቅረብ አልቻሉም፡፡

24. የባለስልጣኑ የስትራቴጅክ ዕቅድ፣ የዓመታዊ ዕቅዱና የዕቅዱ ክንውን ሪፖርቶች ተመጋጋቢ ባለመሆናቸው በየበጀት ዓመቱ ላልተከናወኑት ተግባራት ትኩረት ተሰጥቶት እርምጃ እንዳልተወሰደ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ እያዘጋጀ ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፣

25. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ ሊያደርግ እንዲሁም የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት ዓመቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡

26. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሰኔ 2000ዓ.ም አጠቃላይ የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ / Ethiopia Enivronment out look or the state of environment/ ቢያዘጋጅም እስከ 2004ዓ.ም መጨረሻ ለአካባቢ ምክር ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲሰጥበት /Endorsed/ አለማድረጉ እንዲሁም በ2004ዓ.ም ዘገባ ለማዘጋጀት የሚረዳ በአራት አካባቢዎች ላይ ያተኮረ ማለትም በአብጃታና ሻላ፣ አባያና ጫሞ፣ ግልገል ጊቤ 2 እና የአፋር የግጦሽ መሬትን በተመለከተ ዓመታዊ የአካባቢ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ከማዘጋጀት ውጭ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አጠቃላይ የአከባቢ ሁኔታ ዘገባ ተዘጋጅቶ ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ አልተደረገም፡፡ ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ስድስት የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ውስጥ በኦሮሚያ፣በአማራ፣በድሬደዋና በሐረሪ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በየጊዜው ከሚካሄደው የኢንዱስትሪ መስፋፋት አንፃር በሚደርሰው የአካባቢ ብክለት ላይ እርምጃ ለመውሰድ እና የት አካባቢ ላይ ትኩረት ማድረግ እዳለባቸው በተሟላ ሁኔታ እንዲያውቁ ያላስቻላቸው መሆኑ፤ እንዲሁም ልምድ በመቅሰም በክልሎች

እየደረሰ ያለውን የአካባቢ ብክለት ደረጃ ለማወቅ እንዲያስችል በክልሎች የአካባቢ ዘገባ እንዲዘጋጅ የማያነሳሳ እና የባለስልጣኑን ተሞክሮ በመጠቀም በክልል ደረጃ አዋጆችና ደንቦች እንዳይወጣ ያደረገ ሲሆን በተጨማሪም ወደ ፊት በአካባቢ ላይ ምን አይነት ጉዳት እደሚደርስና ምን አይነት እርምጃ መወሰድ እዳለበት ለማወቅ አለማስቻሉ ታውቋል፡፡

27. ከዚህም በተጨማሪ ባለስልጣኑ እስከ 2004ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የኢንዱስትሪ ብክለትን ለመከላከል በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ በተቀመጠው መሰረት የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ አላዘጋጀም፡፡ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የበካይ ነገሮች መጠንና አወጋገድን የሚያመለክት መረጃ አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

28. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ/BPR/ ጥናት ውስጥ የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየ 3 ዓመቱ ተዘጋጅቶ ይፋ እንደሚደረግ ቢጠቀስም በሰኔ 2000 ዓ.ም የተዘጋጀው እንደ ዓለም አቀፍና አፍሪካ ሀገሮች በፓርላማ ወይም በአካባቢ ኮሚቴዎች ውሳኔ ያልተሰጠበት /Endorsed አለመደረጉን/ እና ከ2000 ዓ.ም በኃላ ተዘጋጅቶ ይፋ ያልተደረገው በሰው ኃይልና በበጀት እጥረት መሆኑን ነገርግን በየዓመቱ የሚሰሩትን ጥናቶች በማደራጀት ለወደፊት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ላይ አንድ አጠቃላይ የአካባቢ ሁኔታና ለውጥ ዘገባ ለማዘጋጀት መታቀዱን፤ እንዲሁም ባለስልጣኑ የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ ያላዘጋጀው ኢንዱስትሪዎች መረጃውን ባለማቅረባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡በዚህ ዙሪያ ባለስልጣን መ/ቤቱ ትኩረት በመስጠት ወቅቱን ጠብቆ የሀገሪቱ የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ እንዲዘጋጅ አለማድረጉን ተገንዝበናል፡፡

## ባለስልጣኑ አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ ማዘጋጀቱን እና በስራ ላይ መዋሉን መከታተሉን በተመለከተ፣

29. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ነገሮችን /ኬሚካሎችን/ ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ ሊያዘጋጅ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

30. ባለስልጣን መ/ቤቱ አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ /አዋጅ እና ደንብ /አላዘጋጀም። እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን አላረጋገጠም። ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት የታዩት 6 የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች እና 46 ኢንዱስትሪዎች በአደገኛ ነገሮች /ኬሚካሎች/ ወይም ዝቃጮች አመራረት፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ የግንዛቤ እጥረት እንዲኖርባቸው እና ወጥ በሆነ መልኩ ይህንን በተመለከተ የሚሰሩ ስራዎችን እንዳይሰሩ አድርጓል።

31. ይህንን በተመለከተ የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናት ተጠይቀው በስራቸው ላሉት ኢንዱስትሪዎች ህጉን ልከው እንዲጠቀሙበት ማድረግ አለመቻላቸው እና በክልል ደረጃ አደገኛ ቆሻሻዎች አሉ ተብሎ ከፋብሪካዎች ጥያቄ በሚቀርብላቸው ጊዜ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት እና ፋብሪካዎች በአካባቢ ላይ ምን አይነት ጉዳት እደሚያደርሱ ለመቆጣጠርና ለመከታተል እንዲሁም የማሻሻያ ሀሳብ ለመስጠት እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል። ይሁን እንጂ የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናትም ሆኑ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መመሪያውን አለማዘጋጀታቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

32. ስለሁኔታው የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎችም ተጠይቀው በሰጡት መልስ የአደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮች ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀም ህግን በተመለከተ እስከ 2004 ዓ.ም ያላዘጋጁ መሆኑን እንዲሁም ባለስልጣኑ ከዘረ ልውጥ ሕያዋን ህግ ውጭ ሌሎች የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ባለመከታተሉና ባለመቆጣጠሩ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸው ፋብሪካዎችና ፕሮጀክቶች ላይ የክትትል ክፍተት ማስከተሉን ገልፀዋል።

33. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 295/95 በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ካዘጋጃቸው 1 የአካባቢ ፖሊሲ፣ 18 ህጎች(አዋጆች፣የዓለም አቀፍ ስምምነቶች የማፀደቂያ አዋጆችና ደንቦችን ጨምሮ)፣9 ደረጃዎች እና 5 መመሪያዎች በድምሩ 33 ፖሊሲዎች፣ህጎች፣ደረጃዎች እና መመሪያዎች ውስጥ 29ኙ (88 በመቶ) የአካባቢ ፖሊሲ፣ ህጎችና መመሪዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለመጀመሩ ታውቋል።እንዲሁም በባለስልጣኑ የተዘጋጁትን የአካባቢ ደረጃዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል የተደራጀ የፍሳሽ መመርመሪያ ላብራቶሪ በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አለመኖሩ ታውቋል።

34. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ላብራቶሪን በተመለከተ መሳሪያዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት ስራ አለመጀመሩን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለወጣው ስምምነት የማፀደቅያ አዋጆችንና ደንቦችን በተመለከተ በባለስልጣኑ ፎካል የሆኑ ሰዎች/Focal person/ ተመድበው እየተከታተሉ መሆኑን፣ለአዋጅ ቁጥር 299/95 ስራ ላይ መዋሉን በ2004ዓ.ም መሰራት ከነበረባቸው አራት ፕሮጀክቶች ውስጥ ለአንድ ፕሮጀክት ብቻ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን፤ ነገር ግን ባለስልጣኑ ፖሊስን የሚከታተለው ፖሊሲውን መሰረት አድርገው የወጡ አዋጆች፣ደንቦች፣ስትራቴጅዎችና መርሐ-ግብሮች መሆናቸውን እና መልስ ላልተሰጠባቸው ነጥቦች ዝርዝሩን ከስርዓት ዝግጅት ዳይሬክቶሬት ክፍል ጠይቀው ምላሽ እደሚሰጡ የገለፁ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

35. ከፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ዓላማና በአዋጅ ቁጥር 295/95 ዓ.ም ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም ከአለም አቀፍ ስምምነቶች አንፃር ባለስልጣኑ ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዳልተወጣ እንዲሁም በ1995 ዓ.ም በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ላይ ስለ አከባቢ ላብራቶሪ ኦዲት ተደርጎ ይሄው ምላሽ የተሰጠ መሆኑ ባለስልጣኑ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ አለመሆኑን ለመገንዘብ ያስችላል፡፡

**የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት ፣ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚረዱ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎችን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት መላኩን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፣**

36. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የአካባቢ ጥበቃ ህግ እና ሕጎቹን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚረዱ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎችን አዘጋጅቶ ለዘርፍ መ/ቤቶችና ለክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች ሊልክ እንዲሁም ክልሎች ለኢንዱስትሪዎች በመላክ በስራ ላይ ማዋላቸውን ሊያረጋግጥ እና ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ/ማምከንን/ በተመለከተ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

37. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና የዘርፍ መ/ቤቶች በተፈራረሙት የውክልና ሰነድ አንቀፅ 1 ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመውሰድ የሚያስችል የአካባቢ ህግ፣ደረጃና መመሪያ እንዲሁም የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ሰነዶች

ለዘርፍ መ/ቤቶች መስጠት እንዳለበት ቢገለፅም ባለስልጣን መ/ቤቱ ለዘርፍ መ/ቤቶቹ በአካባቢ ዙሪያ የወጡትን እና እስከ አሁን ያልፀደቁ የአሰራር መመሪያዎችንና ደረጃዎች በሶፍት ኮፒ ከመላክ ውጭ መመሪያዎቹን አስፀድቆ እንዲጠቀሙበት ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

38. በኦዲቱ ወቅት የታዩት ሶስት የዘርፍ መ/ቤቶች(የማዕድን፣የግብርና እና የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር መ/ቤቶች) እና የሰርቬይ መጠይቅ ተልኮላቸው የመለሱት 6 የዘርፍ መ/ቤቶች የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመውሰድ የሚያስችል መመሪያ ፣የአካባቢ ኦዲትና ከኢንዱስትሪ የሚመነጭ ቆሻሻን በተመለከተ የወጣ መመሪያ አዘጋጅቶ ያልላከ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

39. በዚህም የተነሳ የዘርፍ መ/ቤቶች ምን ዓይነት ፕሮጀክት በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት እና እንደሌለበት በአግባቡ ለማወቅ እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡

40. ይህንን በተመለከተ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በባለስልጣኑ የተዘጋጀው መመሪያ ሣይፀድቅ ለ6ቱ ውክልና ለተሰጣቸው የዘርፍ መ/ቤቶች ብቻ መሰራጨቱን ከመግለፅ ውጭ መመሪያዎቹ ለምን እንዳልፀደቁ ምላሽ አልሰጡም፡፡

41. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ደረጃዎችን ለምሳሌ የባለስልጣን መ/ቤቱ የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295/1995 ደንብና የማስፈፅሚያ መመሪያ፣ በወንዞች፣ በሸለቆዎች እና በሐይቆች ዙሪያ ሊኖር ለሚገባው የማይደፈር ክልል (buffer zone) ደረጃ እና ከተሽከካሪዎች የሚወጣው የጭስ ልቀት ደረጃ፣ለሙቀት ሳቢ ጋዝ ልቀት ደረጃ፣ ለኤሌትሮኒክ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደንብ፣ ለውሃ አዘል መሬቶች እና ሐይቆች አጠቃቀም እና እንክብካቤ አዋጅ ፣ ለአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንብ ፣ለድምፅ ብክለት እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 159/2001 የአፈፃፀም መመሪያዎችን አላዘጋጀም፡፡

42. ባለስልጣኑ 35 የአካባቢ ህጎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ደረጃዎች ቢያዘጋጅም ለክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ከ3 -12 የሚሆኑ ረቂቅ መመሪያዎችን በሶፍት ኮፒ ከመላክ ውጭ የተዘጋጁትን በሙሉ በማፀደቅ አላከም፡፡

43. በዚህም ዙሪያ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በሰጡት አስተያየት ባልፀደቁ እና ህጋዊ መሰረት በሌላቸው መመሪያዎች ለመጠቀም ስጋት የፈጠረባቸው መሆኑንና በአካባቢ ዙሪያ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ያላስቻላቸው እንዲሁም እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ መመሪያዎቹን ለማስተካከልም ሆነ ስለተዘጋጁት መመሪያዎች ግንዛቤ እንዳይኖራቸው

ከማድረጉም በተጨማሪ በስራቸው ላሉት ኢንዱስትሪዎች መመሪያዎቹን አስተላልፈው እንዲጠቀሙበት ለማድረግ እንቅፋት እንደሆነባቸው ገልፀዋል፡፡

44.ኬሚካሎች በአገሪቱ እና በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ ቢሆንም የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ /ማምከንን/ አስመልክቶ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት አላደረገም፡፡

45.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 37ቱ (80%ቱ) ኢንዱስትሪዎች በፋብሪካው ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና መወገድ ያለባቸውን ኬሚካሎች እንዴት ማስወገድ እዳለባቸው፣ የት መውገድ እዳለበት ወይም እንዴት ማምከን እደሚቻል በተደራጀ ሁኔታ ለማወቅ ያላስቻላቸውና ከጊዜ ብዛት ምን አይነት ጉዳት እንደሚያደርሱ ግንዛቤ እንዲያገኙ አንድ ምክንያት እንደሆነባቸው ገልፀዋል ፡፡ ይህም በመሆኑ በመጋዘን ቤቶች እና በየፋብሪካዎች ግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች የተቀመጡ መሆናቸውን፣ ከዚህም በተጨማሪ በየኢንዱስትሪው መጋዘን ቤቶች ውስጥ የተቀመጡት ኬሚካሎች አንዱ ከለሌኛው ተለይቶ ያልተቀመጡና ሌብል/lable/ ያልተደረጉ እንዲሁም በየቦታው ተደፋፍተውና በሙቀት ምክንያት ቀልጠው እንዳሉ ለማየት ተችሏል፡፡



በአየር እጥረትና በሙቀት ምክንያት በመጋዘን ቤት ውስጥ ቀልጠው ከሚገኙ አደገኛ ኬሚካሎች አንዱ(ክሮም)



ከግንዛቤ ማጣት በየቦታው ተደፋፍተው ከሚገኙት ከሚካሎች ሁለቱ

 

የተለያዩ አደገኛ ኬሚካሎች ወይም ጠንካራ አሲዶች (strog Acid) ሌብል ሳይደረጉ እና በየመጋዘን ቤቶች አንዱ ከለሌኛው ሳይለይ አጠገብ ላጠገብ ከተቀመጡት የሁለት ኢንዱስትሪ ለናሙና የቀረበ፡፡

46. ይህንን በተመለከተ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ህጎቹ ተዘጋጅተው በረቂቅ ደረጃ ቢገኙም ከ2002-2004 ዓ.ም ለማስፀደቅ ለሚመለከተው አካል ያልቀረበ መሆኑንና ለወደፊት ግን ረቂቁን ለጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት ለማቅረብ ዝግጅት ላይ መሆናቸውን እንዲሁም ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች አያያዝ ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ /ማምከንን/ ዙሪያ እስካሁን መመሪያም ሆነ ህግ በባለስልጣኑ አለመዘጋጀቱን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለምን እንዳልተዘጋጀ በቂ ምላሽ አልሰጡም፡፡

## የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፣

47. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ምርመራና ውሳኔ አወሳሰድ ላይ ለዘርፍ መ/ቤቶች የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፡፡

48. ለባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 295/95 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ለክልሎች ማድረግ የሚገባውን ድጋፍ ክልሎች ከሚተገብሩት ተግባራት አንፃር በ2002 ዓ.ም በሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ለማስተዋወቅ ለ 2 ቀን ባዘጋጀው አውደ ጥናት እና በ2003 ዓ.ም Integrated Environmental Assessment and Reporting ስልጠና ላይ የአማራ፣ የሐረሪ፣የድሬደዋ እና የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶችን ያላሳተፈ መሆኑ፤ እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ለ 2ቀን በአየር ንብረት ለውጥና በcarbon neutral climate resilient economy /CNCRG/ ባዘጋጀው የስልጣና ፕሮግራም ላይ የኦሮሚያ፣የደቡብ፣የአማራ፣እና የድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶችን ያላሳተፈ መሆኑን እና ለነዚህ ክልሎች ባለስልጣኑ የቴክኒክ ድጋፍ አድርጎላቸው የማያቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

49. ከዚህም በተጨማሪ የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የአማራ፣ የሐረሪ፣ የድሬደዋ እና የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ከ2002-2004 ዓ.ም በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ በአከባቢ አያያዝ ስርዓት፣ በብክለት ቁጥጥር፣ በአካባቢ ኦዲት አደራረግ፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ እና በአደገኛ ኬሚካሎች አጠቃቀም እና አወጋገድ ላይ በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ስልጠና ባለመሰጠቱ ክልሎች በስራቸው ላሉት ኢንዱስትሪዎች ስልጠና መስጠት አለመቻላቸውና ለክትትል አመቺ አለመሆኑን፤እንዲሁም ወጥ የሆነ አሰራር በክልሎችና በባለሙያዎች እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ በአካባቢ ህጎችና ደረጃዎች ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሟላ መልስ ለመስጠት አለመቻላቸውንና በአካባቢ ዙሪያም የክህሎት ክፍተት መፍጠሩን የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናት የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

50. ይህንን በተመለከተ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ እንደየችግሮቻቸው ዓይነት ቅድሚያ መሰጠት ላለበት ክልል እና ችግሮች ቅድሚያ ሰጥተው ስልጠና የሚሰጡ መሆኑን እንዲሁም በ Integrated Environmental Assessment and Reporting ስልጠና ላይ የአማራ፣ የሐረሪ፣የድሬደዋ እና የአዲስ አበባ አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት ባለሙያዎች የተሳተፉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ለክልሎቹና ለችግሮቹ ደረጃ የተሰጠበት ሰነድ እና ሰልጣኞች በስልጠና ላይ መሳተፋቸውን የሚገልፅ የመከታተያ ቅፅ ለኦዲት ቡድኑ እንዲቀርብ ተጠይቆ ይቀርባል የሚል ምላሽ ቢሰጡም ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡

51. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን 22 የዘርፍ መ/ቤቶች ቢኖሩትም ከነዚህ መ/ቤቶች ውስጥ በዝርዝር ኦዲቱ በተከለሱ የስልጠና ሰነዶች መሰረት በ 9 የዘርፍ መ/ቤቶች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 6 የዘርፍ መ/ቤቶች ውስጥ ከአንድ የዘርፍ መ/ቤት ውጭ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ምርመራና ውሳኔ አወሳሰድ ላይ ለ14ቱ (58%) የዘርፍ መ/ቤቶች ግንዛቤ እንዲያገኙ በአዋጅ ቁጥር 295/95 መሰረት በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጥቷቸው እንደማያውቅ ታውቋል፡፡

52. ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ ለተመለከታቸው 3 የዘርፍ መ/ቤቶች ባለስልጣኑ ከ 2002-2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በ 2003 አንድ ጊዜ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስልጠና ከመስጠት ውጭ በ2002 እና በ2004 ዓ.ም ምንም ዓይነት ስልጠና ያልሰጣቸውና የቴክኒክ ድጋፍም ያላደረገላቸው

መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ ውክልና የተሰጣቸው 3ቱ የዘርፍ መ/ቤቶች በውክልና ላይ የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች ለመወጣት መቸገራቸውን ገልፀዋል፡፡

53. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በ2003 ዓ.ም ውክልና ለተሰጣቸው ለ6 የዘርፍ መ/ቤቶች እና ስልጠና ላይ እንዲሳተፉ ለ2 ሚኒስቴር መ/ቤቶች ባለስልጣኑ ደብዳቤ መላኩን ከመግለፅ ውጭ ለሌሎች የዘርፍ መ/ቤቶች እንዲሳተፉ ያልተደረገበት ምክንያት አልገለፁም፡፡

## II. ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

### የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣

54. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት ሊሰራ እና የሪፖርት አቀራረብና አደራረግን በተመለከተ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ (memorandum of understanding) ሊኖረው እንዲሁም የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

55. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት 6 የክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች እና በስራቸው ካሉት 46 ፋብሪካዎች እንዲሁም 8 የዘርፍ መ/ቤቶች ጋር ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት እንደማይሰራ ታውቋል ፡፡

56. በዚህም ምክንያት የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ዕቅዶችን በጋራ እንዳያቅዱና ግብረ መልስ እንዳይኖራቸው ማድረጉ፣ የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት እንዲሁም በአካባቢ ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት አለማስቻሉ እና በየክልሉ በአካባቢ ዙሪያ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር ማድረጉን የደቡብ፣የአማራ፣የሐረሪና የኦሮሚያ ክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናት የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

57. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የደቡብ፣ የአዲስ አበባ፣ የኦሮሚያ፣ የድሬደዋ፣ የሐረሪና የአማራ ክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች እና የማዕድን ፣ የግብርናና የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እንዲሁም በሰርቬይ መጠይቅ ተልኮላቸው የመለሱት 6

መ/ቤቶች ከፌዴራል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ጋር የሪፖርት አደራረግን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ /MOU/ እንደሌላቸው ታውቋል፡፡

58. ይህም በመሆኑ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በየክልሎቹ በአካባቢ ዙሪያ የተከናወኑትን ስራዎች ለፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለማሳወቅ እንቅፋት የሆነባቸው መሆኑን ውክልና የተሰጣቸውም ሚኒስቴር መ/ቤቶች በየጊዜው በሪፖርት ላይ ጠቅሰው የሚልኳቸው ችግሮች መፍትሔ ያላገኙ መሆኑና በውክልናው ላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በአግባቡ ለመፈፀም ክፍተት የፈጠረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

59. ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

60. ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ክልሎች የኦሮሚያ፣ የድሬደዋ፣ የሐረሪ፣ የደቡብ፣ የአዲስ አበባ እና የአማራ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች እና በስራቸው ያሉት 46 ፋብሪካዎች እንዲሁም ውክልና የተሰጣቸው 3 የዘርፍ መ/ቤቶች እና ውክልና ያልተሰጣቸው የሰርቨይ መጠይቅ ተልኮላቸው የመለሱት 6 የዘርፍ መ/ቤቶች ላይ በአካባቢ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ የሚፈለገው መረጃ በሚፈለገው ፍጥነት ለማግኘትና በሀገሪቱ ያሉት ኢንዱስትሪዎች መረጃ፣ ዓይነት፣ ብዛት፣ አካባቢ ለማወቅ አለማስቻሉን፤ በዘርፍ መ/ቤቶች በአካባቢ ጥበቃ መረጃ ላይ እኩል ግንዛቤ እንዳይኖር አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠሩን እንዲሁም የዘርፍን መ/ቤት ለባለስልጣኑ ተባባሪ ለመሆን አለማስቻሉን እና ወቅታዊ የሆኑና በአካባቢ ዙሪያ የወጡ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን እና መመሪያዎችን ከአካባቢ ጥበቃ ሁኔታዎች አንፃር ለመገንዘብና እርምጃ ለመውሰድ እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡

61. ስለ ጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ተጠሪነታቸው ለየክልላቸው እንጂ ለፌዴራል ስላልሆነ እንዲሁም ከሴክተር መ/ቤቶችና ከዘርፍ መ/ቤቶች ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ባለመኖሩ ምክንያት በሚያገናኛቸው ነገሮች ከመገናኘት ውጭ መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን እንደማያዘጋጁ፣ የሪፖርት አደራረግ ስርዓት ባለመዘርጋቱ ምክንያት የሪፖርት አደራረግን በተመለከተ ባለስልጣኑ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ እንደሌለው እና የአካባቢ መረጃ ስርዓቱን ለመዘርጋት ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ የነበረ ቢሆንም በባለሙያዎች ከስራ መልቀቅ፣በበጀት እና በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ስርዓቱ ተዘርግቶ አለመጠናቀቁን፡ ከዚህም የተነሳ ቀልጣፋና በቂ የሆነ የመረጃ ልውውጥ እንዳይኖር ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

**የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና የዘርፍ መ/ቤቶች የክትትልና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የሚልኩለት መሆኑን በተመለከተ፣**

62. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን በተመለከተ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እድያሳውቁት ሊያደርግ እንዲሁም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የዘርፍ መ/ቤቶች /የሚኒስቴር መ/ቤቶች/ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እዲልኩለት ሊያደርግ እና በተሰጣቸው ውክልና መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

63. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ለታዩት ለኦሮሚያ፣ለደቡብ፣ለአዲስ አበባ፣ ለድሬደዋ፣ ለሐረሪና ለአማራ ክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት በመዘርጋት እድያሳውቁት አላደረገም፡፡

64. የአዲስ አበባና የድሬደዋ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትል ሪፖርት ማድረግን በተመለከተ ከፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንደቅደምተከተላቸው በ2003 ዓ.ምና በ2004 አጋማሽ ላይ ውክልና ቢሰጣቸውም ለባለስልጣኑ የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት የክትትል እና የቁጥጥር ሪፖርቶችን አቅርበው የማያውቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

65. የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናት በዚህም ዙሪያ ተጠይቀው ጠያቂ አካልና የሚያስገድድ ሁኔታም ሆነ ስምምነት አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ከዚህም የተነሳ ሁለቱ ውክልና የተሰጣቸው የከተማ አስተዳደሮች እና ውክልና ያልተሰጣቸው 9ኙ ክልሎች ሪፖርት የማይልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

66. በ2003 ዓ.ም ለውሃና ኢነርጅ፣ ለግብርና እና ለማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቶች /የዘርፍ መ/ቤቶች /ባለስልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በየሩብ ዓመቱ እንዲልኩለት ቢያደርግም የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂ አስተላልፎ አያውቅም፡፡ እንዲሁም ባለስልጣኑ የዘርፍ መ/ቤቶች በተሰጣቸው በውክልና በተቀመጠው መሰረት ስራውን ስለመስራታቸው የማያረጋግጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

67. የውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር ለ2 ፕሮጀክቶች፣ የግብርና ሚኒስቴር ለ 9 ፕሮጀክቶች እና የማዕድን ሚኒስቴር ለ38 ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ገምግመው የይሁንታ ፈቃድ የሰጡ ቢሆንም በውክልናው አንቀፅ 1 ተራ ቁጥር 2 መሰረት የማዕድን

ሚኒስቴር ለ 7ቱ ባለፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሲያካሄዱ የጥቅም ግጭት እንዳያስከትል የሚኒስቴር መ/ቤቱን ወይም የፌዴራልም ሆነ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ሠራተኞችን ያላሳተፈ መሆኑን በማረጋገጫ ሰሪትፍኬት በፊርማ እንዲያረጋግጡ ከማድረግ ውጭ ለ42 ባለፕሮጀክቶች ሳያረጋግጡ ወደ ስራ የገቡ መሆኑ ታውቋል ፡፡

68. ይህም የሆነው የዘርፍ መ/ቤቶች በየ3ወሩ የሚልኩትን ሪፖርት እና የጥናት ሰነድ ቅጂ በሶፍትና በሃርድ ኮፒ ከመቀበል ውጭ ባለስልጣኑ በውክልናው ላይ በተቀመጡ ዝርዝር ተግባራት መሰረት ስለመሰራታቸውና ስላለመሰራታቸው ክትትል ባለማድረጉ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

69. ስለጉዳዩ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ባለስልጣኑ የሪፖርት አደራረግ ስርዓት ባለመዘርጋቱ የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን በተመለከተ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እንዲያሳውቁት አለማድረጉን እንዲሁም የክትትል ሪፖርቶችንም በየወቅቱ ተከታትሎ የማይቀበል መሆኑንና በዚህም ምክንያት ጥቅል የሆነ ሀገራዊ ሪፖርት ለማዘጋጀትም ሆነ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ እንዳላስቻላቸው እንዲሁም ከ2003 ዓ.ም በፊት በባለስልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ገምግሞ የይሁንታ ፈቃድ የሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ዝርዝር በተደጋጋሚ ተጠይቀው ለመጠይቁ ተገቢውን ምላሽ አልሰጡም፡፡

## III. የአካባቢ አሃድ/Enivronmental unit/ በዘርፍ መ/ቤቶች መቋቋሙን እንዲሁም በወጡ የአካባቢ ስርዓት አተገባበር ላይ ለኢንዱስትሪዎችና ለባለድርሻ አካላት የሚደረገው ክትትልና ግምገማ ብቃት ባለው መልኩ መደረጉን በተመለከተ፡

### የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አሃድን የሚከታተል ክፍል ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች እንዲያቋቁሙ ማድረጉን በተመለከተ፣

70. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አሃድን/የአካባቢ ነክ ጉዳዩችን የሚከታተል ክፍል/ ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች እንዲያቋቁሙ ሊያደርግ እንዲሁም የስራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ስልጣን የፌደራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአከባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ሊገመግም፣ የይሁንታ ፈቃድ ሊሰጥ፣ ሊከታተል እና በሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ስለመስራታቸው ሊያረጋግጥና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

71. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን 24 የዘርፍ መ/ቤቶች ቢኖሩትም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 3 የሚኒስቴር መ/ቤቶችና መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት 6 የዘርፍ መ/ቤቶች ውስጥ በ2003 ዓ.ም የግብርና፣ የውሀና ኢነርጂ እና የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቶች ብቻ ባለስልጣኑ የአካባቢ አሃድ እንዲያቋቁሙ ያደረገ ሲሆን በ2005 ዓ.ም በኢንዱስትሪ፣ በስራና ከተማ ልማት ና በትራንስፖርት ሚኒስቴር መ/ቤቶች ለማቋቋም ጥረት ያደረገ ቢሆንም በ18ቱ (75%) የዘርፍ መ/ቤቶች የአካባቢ አሃድ/የአካባቢ ነክ ጉዳዮችን የሚከታተል ክፍል/ እንዲያቋቁሙ አላደረገም፡፡እንዲሁም በናሙና ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 27ቱ ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ አሃድ ያላቋቋሙ ሲሆኑ፣16 ቱ ደግሞ በኮሚቴ ከሌላ ክፍል ስራ ጋር በተደራቢነት ከመስራት ውጪ ራሱን የቻለ የአካባቢ ነክ ጉዳዩችን የሚከታተል ክፍል /የአካባቢ አሃድን/ እንዳላቋቋሙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ይህም በመሆኑ በአካባቢ ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዳይሰጥበት እና በእያንዳንዱ ፋብሪካ አካባቢን የሚመለከቱ ጉዳዩች የሚከታተል አካል እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ ፋብሪካዎች በየክልላቸው ከሚገኙ ከአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር እንዳይሰሩ ማድረጉን የፋብሪካዎቹ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

73. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ስልጣን የፌደራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ እንዲገመግሙና በይሁንታ ፈቃዱ መሰረት ስለመስራታቸው እንዲከታተሉ፣ እንዲቆጣጠሩና እንዲያረጋግጡ ለግብርና፣ለውሃና ኢነርጅ እና ለማዕድን ሚኒስቴር በ2003ዓ.ም አጋማሽ ውክልና የሰጠ ቢሆንም ከ2003 ዓ.ም በፊት የይሁንታ ፈቃድ የተሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ዝርዝርና የጥናት ቅጅያቸውን ከውክልናው ጋር ለሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ባለማስተላለፉ በአካባቢ ተፅዕኖ ሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ፕሮጀክቶቹ ስለመስራታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ክትትልም ሆነ ቁጥጥር አላደረገም፡፡ ከ2003 ዓ.ም በፊት በባለስልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ተገምግሞ የይሁንታ ፈቃድ የሰጣቸው ፕሮጀክቶች ዝርዝር በተደጋጋሚ በኦዲት ቡድኑ ቢጠየቅም ሊቀርብ አልቻለም፡፡

74. ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንም እስከ 2004ዓ.ም በአንድ ፕሮጀክት ላይ ብቻ ተከታትሎ በሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ስለመስራቱ በማረጋገጥ ቁጥጥር ከማድረግ ውጭ በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል በማድረግ በግዴታው መሰረት ስለመስራታቸው ያላረጋገጠ እና ያልተቆጣጠረ መሆኑ ታውቋል፡፡

75. ስለ ሁኔታው ውክልና የተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች ተጠይቀው ከ2003 ዓ.ም በፊት የይሁንታ ፈቃድ የተሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ዝርዝርና የጥናት ቅጅያቸውን ከውክልናው ጋር ባለስልጣኑ ባለማስተላለፉ በአካባቢ ተፅዕኖ ሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ፕሮጀክቶቹ ስለመስራታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ክትትልም ሆነ ቁጥጥር ለማድረግ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

76. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች የአካባቢ አሃድ ያልተቋቋመበት ምክንያት በባለስልጣኑ ስራው በቅርብ ጊዜ በመጀመሩ ምክንያት እንደሆነና ከሶስቱ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ውጭ በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች ለማቋቋም ጥረት እየተደረገ መሆኑን እንዲሁም በተቀሩት የዘርፍ መ/ቤቶችም የአካባቢ አሃድ እንዲቋቋም አለመደረጉ በባለስልጣኑ ላይ የስራ ጫና እንደሚፈጥር እንዲሁም ለማዕድን ሚኒስቴር በጥያቄያቸው መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነዶች ኮፒ ተደርጎ ተልኳል የሚል ምላሽ ቢሰጡም ስለመላኩ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

## የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ግምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ማሳወቁን በተመለከተ፣

77. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ግምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

78. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ ገምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ ማሳወቅ እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 295/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 5 ቢገለፅም በኦዲቱ ወቅት በአካል ከታዩና ውክልና ከተሰጣቸው የዘርፍ መ/ቤቶች ውስጥ የግብርና እና የማዕድን ሚኒስቴር መ/ቤቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ቅጅ በሶፍት ኮፒ እና በሃርድ ኮፒ በየሶስት ወሩ ከሪፖርት ጋር የሚልኩ ቢሆንም የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለነዚህ ፈቃድ ሰጪ ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ እንደማያሳውቃቸው ታውቋል፡፡ከዚህም የተነሳ ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ በግምገማው ላይ ያላቸውን ክፍተት ለማወቅ እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡

79. በዚህም ዙሪያ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ግምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ማሳወቁን በተመለከተ የዘርፍ መ/ቤቶቹ እንዲሰሩ በውክልና ስላስተላለፈ መስራት

እንደሌለበት ገልፀዋል፡፡ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት እንዳልተወጣ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ባለስልጣን መ/ቤቱ ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፣

80. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የሰጣቸው ኢንዱስትሪዎችን በአካባቢ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ሊከታተልና ቁጥጥር ሊያደርግ ወይም ክልሎች እንዲከታተሉ እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ በውክልና ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

81. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ2004 አጋማሽ ወር በኂላ የስርዓት ተከባሪነትን ለማረጋገጥ እና ለመስክ ስራ ባለሙያዎችን ባሰማራበት ወቅት ከስምንት የኢንዱስትሪ ዘርፎች (ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ፣ ሲሚንቶ፣ ኬሚካል፣ ስኳር፣ ብረታ ብረት፣ ምግብና መጠጥ እና ማተሚያ ቤቶች) ውስጥ በሶስቱ ብቻ (በምግብ፣በኬሚካል እና በብረታብረት ኢንዱስትሪዎች) በ21 ፋብሪካ የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን የማረጋገጥ ስራ ቢጀምርም በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ፣ በአማራ፣ በድሬደዋ እና በሀረር ክልሎች በናሙና ተወስደው ከታዩት 46 ፋብሪካዎች ውስጥ 40ዎቹ (87%) የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ባለስልጣኑ አላረጋገጠም፡፡ከዚህም በተጨማሪ ከ40ዎቹ ውስጥ 32ቱ ፋብሪካዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማም ሳያስገመግሙ ስራ መጀመራቸው ታውቋል፡፡ይህም በመሆኑ እነዚህ ፋብሪካዎች ስለ አካባቢ አጠባበቅ እና ስለ አካባቢ ኦዲት ግንዛቤ እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡

82. በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት በአግባቡ ማድረጋቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንደማያረጋግጥ እና ላረጋገጠውም የግብረ መልስ ሪፖርት እንደማይልክ ታውቋል፡፡

83. በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋና በሐረሪ ክልል ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከፌደራል ንግድ እና እንዱስትሪ ሚኒስቴር የስራ ፈቃድ ያገኙ 33 ፋብሪካዎች ቢኖሩም፤ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እራሱ ያልተከታተለ ወይም ከአዲስ አበባና ከድሬደዋ ክልሎች ውጭ ለሁሉም የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በየክልላቸው ለሚገኙ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸውን ኢንዱስትሪዎች ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ውክልና ያልሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

84. ይህም በመሆኑ በ4ቱ ክልሎች ከፌደራል ንግድ እና እንዱስትሪ ሚኒስቴር የስራ ፈቃድ ካገኙ 22 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 18 (82%) ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎባቸው አያውቅም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የፌዴራል

አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በራሱ ባለመከታተሉና ባለመቆጣሩ ወይም ለክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናት ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ውክልና ባለመስጠቱ እና ከፌዴራል የስራ ፈቃድ ያገኙትን ኢንዱስትሪዎች ዝርዝር ለክልሎች ባለማስተላለፉ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

85. በዚህ ዙሪያ የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አስገምግመውና ሳያስገመግሙ ወደ ስራ የገቡትን እና በፌዴራል ደረጃ የስራ ፈቃድ አግኝተው በክልሎች እየሰሩ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ብክለት ደረጃቸውን ፣ ምን ዓይነት ኬሚካል እንደሚጠቀሙ እና ምን ዓይነት በካይ ነገር ወደ ወንዞችና ሐይቆች እንደሚለቁ ለማወቅ አለማስቻሉን እንዲሁም በአካባቢ አጠባበቅና አያያዝ ዙሪያ በየኢንዱስትሪው ያሉትን ችግሮች ለይተው በወቅቱ የሚፈልጉትን ሙያዊ እገዛና የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡

86. በኦዲቱ ወቅት ከተጎበኙት ፋብሪካች ውስጥ 9 ፋብሪካዎች የኬሚካል ማስቀመጫ መጋዘን ቤታቸው በቂ አየር የማያስገባ መሆኑን፣23 ፋብሪካዎች ኬሚካሎች በሰራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ እገዛ የሚያደርግ ማቴሪያል ሰፍቲ ዳታ ሽታቸው/Material safety data sheet/ አብሮ አለማስቀመጣቸው፣ 9 ፋብሪካዎች በግቢው ውስጥ ከፍተኛ ሽታ ያላቸው የቆዳ ቁርጥራጭ፣ ፀጉር፣ ስላጆችን(slage) እና አደገኛ ኬሚካሎችን ለፋብሪካው ሰራተኞች ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በግቢያቸው፣ በመጋዘን ቤቶች አካባቢና ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ

ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ፋብሪካዎቹ በአካባቢው ላይ የሚለቁአቸው ፍሳሾች በየጊዜው የፍሳሽ ምርመራ/ቴስት/ ሳይደረጉ እንደሚለቁ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ ያላቸውን ክፍተት እንዳያሚሉ እና ያሉበትን ደረጃ እንዳያውቁ እንቅፋት እንደሆነባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡




የኬሚካል ማስቀመጫ መጋዘን ቤታቸው በቂ አየር ከማያስገቡ ፋብሪካዎች ውስጥ አንዱ



ከፍተኛ ሽታ ያላቸው የቆዳ ቁርጥራጭ፣ ፀጉር፣ ስላጆችን(slage) እና አደገኛ ኬሚካሎች ለፋብሪካው ሰራተኞች ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በየፋብሪካዎቹ ግቢ ውስጥና በየአካባቢው ተበታትነው ከሚገኙ ጥቅቶቹ

87.ስለሁኔታው የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የማረጋገጡ ዓላማ ስንት ኢንዱስትሪዎች ኦዲት መደረጋቸውን እና አለመደረጋቸውን ለማወቅ እንጅ ኦዲት ለተደረጉት ግብረ መልስ ለመላክ እንዳልሆነ እና ግብረ መልስም የማይልኩ መሆኑን እንዲሁም ለሁሉም የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በየክልላቸው የሚገኙ እና በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸውን ኢንዱስትሪዎች ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ፈቃደኛ ስለመሆናቸው በስብሰባ ወቅት ጥያቄ አቅርቦ የነበረ መሆኑን፣ሆኖም ከአዲስ አበባና ከድሬደዋ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ውጭ የተቀሩት 9 ክልሎች ውክልና እንዲሰጣቸው ባለመጠየቃቸው ምክንያት በራሱ ውክልና አለመስጠቱን ገልፀዋል፡፡ ይህም በመሆኑ በዘጠኙም ክልሎች የሚገኙ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች እስከ 2004 ዓ.ም ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

## የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸቱን በተመለከተ፣

88. ባለስልጣን መ/ቤቱ ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች በሰው፣ በእንስሳት እዲሁም በእፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

89. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸው በካይ ኬሚካሎች በሰው፣ በእንስሳት እዲሁም በእፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ክትትል እያደረገ ለሚመለከተው አካል በማሳወቅና የኬሚካል አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት የሚወገዱበትን ሁኔታ አላመቻቸም፡፡

90. የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች በአደገኛ ኬሚካሎች ዙሪያ ለፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኬሚካሎቹን አወጋገድ በተመለከተ ሁኔታዎችን እንዲያመቻችላቸው ወይም የአደገኛ ኬሚካሎች ህግና መመሪያ እንዲልክላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ባለስልጣኑ ለ2 ድርጅቶች ብቻ አወጋገዱን በተመለከተ የተለየ ሁኔታ የሚኖር ከሆነ ለወደፊት እንደሚያሳውቃቸው በደብዳቤ ከመግፅ ውጭ መፍትሄ ያልሰጣቸው በመሆኑ በአወጋገድ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡

91. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በሐረሪ፣ በአዲስ አበባና በድሬደዋ ክልሎች እና የአማራ ገጠር መሬትና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በየክልሉ ያሉትን የአደገኛ ኬሚካል ዳታ ለማሰባሰብ ከጀመረው መረጃ በተገኘው መሰረት ከ1 እስከ 20 ዓመታት ያስቆጠሩ በ16 ፋብሪካዎች 314,565 ኪ.ግ፣ 280,207 ሊትር፣ 7,059,523 በቁጥር፣ 140,450 ዶዝ፣ 1,506 ቲዩብ፣ 764 ፓኬትና 25 ጋሎን እንዲሁም የተለያዩ መጠን ያላቸው 5,290 በርሜል፣ 2,373 ጀሪካን፣ 10,578 ከረጢት፣ 527 ካርቶን፣ 9,548 ቆርቆሮ፣ 712 ጠርሙስና 90 ሳጥን የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፉና የሚወገዱ ኬሚካሎች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ኬሚካሎች ግማሻቸው ለአካባቢና ለሰዎች ጥንቃቄ ባልተደረገበት ሁኔታ የተቀበሩና በመቀበር ሂደት ላይ ያሉ የተቀሩት ደግሞ በየመጋዘን ቤቶቹ አካባቢ ተቀምጠው አካባቢውን በመጉዳት ላይ ሲሆኑ ለፍንዳታ የሚያገለግል /ካርባይድ/፣ክሎሪን ጋዝ፣ የማላታይን ዱቄት፣ ዲዲቲ፣ ሰልፈሪክ አሲድ፣ ሊድ፣ እና ሌሎች ዓይነቶች አደገኛ ኬሚካሎች ይገኙባቸዋል፡፡





ለአካባቢና ለሰዎች ጥንቃቄ ባልተደረገበት ሁኔታ በፋብሪካዎች አካባቢ ከሚገኙ ከሚካሎች ጥቂቶቹ

ለፍንዳታ የሚያገለግል ኬሚካል/ካርባይድ/





በየኢንዱስትሪው አካባቢውን መጉዳት ላይ ከሚገኙ አደገኛ ከሚካሎች ጥቂቶቹ

92. ከዚህም በተጨማሪ በ 2 ፋብሪካዎች በውስጣቸው የሜሪኩሪና ሰልፈሪክ አሲድ ይዘት ያላቸው የተበላሹ 359 የመኪና ባትሪና 13,384 የፍሎሬሰንት ላምፕ ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም በ 5 ፋብሪካዎች ቁጥራቸውና ዓይነታቸው በውል የማይታወቁ ብዛት ያላቸው በየመጋዘን ቤቶቻቸው ዙሪያና ውስጥ ታሽገው የተቀመጡ ኬሚካሎች ተዝረክርከው ዕቃዎቻቸው እየተበሉ፣በአካባቢው ላይ ከፍተኛ ሽታ እየፈጠሩ እና እየጎዱ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

93. አንድ ፋብሪካ ደግሞ ቁጥራቸው የማይታወቅ የመኪና ባትሪና የፍሎሬሰንት ላምፕ በግቢው ውስጥ በማቃጠልና የመቅበር ስራ ላይ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡





በየፋብሪካው አካባቢው ላይ ከፍተኛ ሽታ የፈጠሩ እና የተቀመጡበትን ዕቃና በትነት አማካኝነት የመጋዘን ቤቶቹን ጣራ ከጎዱ አደገኛ ኬሚካሎች ጥቅቶቹ

94. በእነዚህ ችግሮች ዙሪያ  የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ሙያዊ መፍትሄም ሆነ ግንዛቤ ለመስጠት ያልቻሉ ሲሆን የየፋብሪካዎቹ ሠራተኞች በየፋብሪካው አካባቢ የሚገኙ ኬሚካሎች በሰው፣በእንስሳትና በአካባቢ ላይ ለወደፊት ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ የሚል ስጋት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

95. ስለጉዳዩ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በኬሚካል አወጋገድ ዙሪያ ሕግም ሆነ መመሪያ ስላልተዘጋጀ ለሌላ አካል አለማሳወቃቸውን እና ለሁለት ድርጅቶች ብቻ የተለየ ሁኔታ እስኪፈጠር ኬሚካሎቹ ተለይተው እንዲቀመጡ በደብዳቤ ማሳወቃቸውን ገልፀዋል፡፡

## የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፋብሪካዎች የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ  ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፣

96. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ ሊወገድ የማይቻል ከሆነ ይህንን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

97. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነባር ፋብሪካዎች የሚያስከትሉት ሊወገድ የማይችል አሉታዊ ተፅእኖ ሲኖር በደንብ ቁጥር 159/2001 በተቀመጠው የ5 አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያስወግድ የሚያስችል አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ እርምጃ ወስዶ አልተገኘም፡፡

98. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በድሬደዋ፣ በሀረር እና በአዲስ አበባ ክልሎች ከ46 ፋብሪካዎች ውስጥ 35ቱ ነባር ፋብሪካዎች ሲሆኑ ከፋብሪካዎቹ እንቅስቃሴ በሰዎች፣ በእፅዋት እንዲሁም በእንስሳት ላይ በሚከሰተው አሉታዊ ተፅእኖ ላይ ባለስልጣኑ በአምስት አመቱ የጊዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅኖው እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ ምንም አይነት አስተዳደራዊም ሆነ ህጋዊ እርምጃ ወስዶ አያውቅም፡፡ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችም ነባር ፋብሪካዎች የሚያስከትሉትን አሉታዊ ተፅእኖ በመከታተል እርምጃ እንዲወስዱ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR) ሰነድ ላይ ክልሎች እንደሚከታተሉ ለአንድ ፋብሪካ  በደብዳቤ ከመግለፅ ውጪ የነባር ፋብሪካዎችን ስም ዝርዝር ለክልሎች በማስተላለፍ እርምጃ እንዲወስዱ አላደረገም፡፡

99. በህዝብ አቤቱታ እና ቅሬታ መሰረት በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ  እና በድሬደዋ  አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች አሉታዊ ተፅኖውን ለመቀነስ የሚያስችል አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ

ጅማሮው ቢኖርም በተቀሩት ስምንት ክልሎች እና በነዚሁ ክልሎች ስራው ተጠናክሮ እንዲሰራ ባለስልጣኑ ጥረት አላደረገም፡፡

100. በኦዲቱ ወቅት በስድስቱ ክልሎች የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ፣ የሲምንቶ፣ የኬሚካል፣ የስኳር፣ የምግብና የመጠጥ፣ የማተሚያ ቤት እና የብረታብረት ኢንዱስትሪዎችን የሚያጠቃልል 46 ፋብሪካዎች ውስጥ 26ቱ ፋብሪካዎች የፍሳሽ ማጣሪያ እና የአቧራና የጭስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ የሌላቸው በመሆኑ ከፋብሪካው የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም በቱቦ በመጠቀም ወደ አቃቂ፣ ሰበታ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ-ወርቃማ እና አባይ ወንዞች እና ወደ ገበሬዎች ማሳ ቀጥታ የሚለቀቅ መሆኑን እንዲሁም ፍሳሹ ጉድጓድ በመቆፈር ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ መደረጉ ከዚህም ባሻገር የፍሳሹ ውሃ በትነት መልክ ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑን እና ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚወጣው ጭስ እና ብናኝም ወደ አየር የሚለቀቅ መሆኑ ታውቋል፡፡



ከፋብሪካዎች የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም በቱቦ በመጠቀም ወደ አቃቂ ፣ ሰበታ ፣ ሞጆ ፣ ኮምቦልቻ-ወርቃማ እና አባይ ወንዞች ከሚለቀቁት ውስጥ ጥቂቶቹን



ከፋብሪካዎች የሚወጣው ፍሳሽ ሳይታከም ወደ ገበሬዎች ማሳ ቀጥታ ከሚለቀቁት ውስጥ አንዱ




ከፋብሪካዎች የሚለቀቀው ፍሳሽ ከፍተኛ የሆነ አደገኛ አሲዶችን የያዘ መሆኑን ከሚያሳዩ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ





ከፋብሪካዎች የሚወጣው ፈሳሽ ቆሻሻ ሳይታከም ጉድጓድ በመቆፈር ፍሳሹ ወደ መሬት ውስጥ እንዲሰርግ እና የፍሳሹ ውሃ በትነት መልክ ወደ አየር ከሚለቀቁት ውስጥ ሁለቱን



ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች የጭስ እና የሲሚንቶ ብናኝ ወደ አየር ከሚለቀቁ አንዱ

101. የተቀሩት 9ኙ ፋብሪካዎች ደግሞ የመጀመሪያ የማጣሪያ መሳሪያ ቢኖራቸውም በፍሳሽ ማስቀመጫነት የሚጠቀሙበት ገንዳ የሰዎች መኖሪያ ቤቶች ያሉበት እና ከብቶች ሳር የሚግጡበት አካባቢ መሆኑ በተጨማሪም የBOD /Biochemical Oxygen Demand/ እና COD /Chemical Oxygen Demand/ ቴስት ሳይደረግ በፍሳሾቹ ውስጥ አደገኛ ኬሚካሎች እንደክሮም፣ሰልፈሪክ አሲድ፣ሰሊፋይድ ደረጃቸው ሳይታወቅ በአካባቢው በሚገኘው ትናንሽ ወንዞች ላይ የሚለቀቁ መሆኑ እንዲሁም በፋብሪካዎቹ ግቢ ውስጥ ያሉ የፀጉር፣የቆዳ ቁርጥራጮች፣ስላጅ እና ሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች የኬሚካል ይዘት ያላቸው ቢሆንም ለአካባቢው ህዝብ እና ለሰራተኞች ጥንቃቄ ባልተደረገበት ሁኔታ በግቢው ውስጥ መቃጠሉ እና ተዝረክርኮ መገኘቱ ታውቋል፡፡

  

*ፋብሪካዎች በፍሳሽ ማስቀመጫነት የሚጠቀሙበት ገንዳ የሰዎች መኖሪያ ቤቶች ያሉበት እና ከብቶች ሳር የሚግጡበት አካባቢ መሆኑን ከሚያሳዩ ፎቶዎች ውስጥ የአንዱ*

102. በአካባቢው እና በህዝቡ ላይ ፋብሪካዎቹ እያስከተሉ ያሉት አሉታዊ ተፅእኖ ላይ እርምጃ አለመወሰዱ እና የህዝቡ አቤቱታ እና ቅሬታ ምላሽ ማግኘት አለመቻሉ፤ እንዲሁም በየአካባቢው የሚገኙ ሰዎች፣ አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎች እና እንስሳት ላይ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጉዳት እያስከተለ መገኘቱን የክልል አካባቢ ጥበቃ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

103. ስለጉዳዩ የባለስላጣኑ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለኢንዱስትሪዎች የተሰጠው የእፎይታ ጊዜ ባለመድረሱ ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

104. በአካባቢ እንክብካቤ ስርዓት አተገባበርና ክትትል እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራር አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና በክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም ለባለስልጣኑ በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር አንጻር ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ እንክብካቤ ሥርዓት አተገባበር፣ ክትትልና ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ያሉበት መሆኑ ታውቋል፡፡

105. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በስትራቴጂክ ዕቅድ ያቀዳቸውን ስራዎች በተሟላ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅድ በማካተት ተግባራዊ አለማድረጉ፤በየጊዜው በሚያዘጋጀው የእቅድ ክንውን ሪፖርት መሰረት ለሚታዩ ክፍተቶች ለማስተካከል በተሟላ መልኩ እርምጃ አለመውሰዱ፤

106. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አጠቃላይ የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ ያላዘጋጀና ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ ያልተደረገ ሲሆን በሰኔ 2000 ዓ.ም የተዘጋጀውም ዘገባ በአካባቢ ምክር ቤት ውሳኔ ያልተሰጠበት /ኢንዶርስ ያልተደረገ/ መሆኑ እንዲሁም የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ አለማዘጋጀቱ፤

107. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ አለማዘጋጀቱ፤ እንዲሁም የፀደቁ የአካባቢ ፖሊሲ፣ህጎች፣ደረጃዎች እና መመሪያዎችን ስራ ላይ መዋላቸውን ባለስልጣኑ የማረጋገጥም ሆነ የክትትልና የቁጥጥር ስራ አለመስራቱን፤

108. ባለስልጣኑ ለዘርፍ መ/ቤቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመውሰድ የሚያስችል መመሪያ በሶፍት ኮፒ ከመላክ ውጭ ሙሉ በሙሉ አዘጋጅቶና አስፀድቆ ያልላከ መሆኑን እና የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ደረጃዎችን ቢያዘጋጅም በማፀደቅ ለክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች /ኤጀንሲዎች/ አለመላኩ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች አያያዝን አጠቃቀምንና አወጋገድን አሰመልክቶ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት አለማድረጉ፤

109. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለሁሉም ክልሎች እና የዘርፍ መ/ቤቶች በተሟላ መልኩ ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ያልሰጠ መሆኑ፤

110. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት አለመስራቱ እና የሪፖርት አደራረግን በተመለከተ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ (memorandum of understanding) የሌለው መሆኑ፤እንዲሁም የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት አለመዘርጋቱ፤

111. ፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን በተመለከተ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በየሩብ ዓመቱ እድያሳውቁት አለማድረጉ። እንዲሁም ባለስልጣኑ የዘርፍ መ/ቤቶች በውክልና በተቀመጠው መሰረት መስራታቸው የማያረጋግጥ መሆኑ፤

112. ባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ አሃድን ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች እንዲያቋቁሙ አለማድረጉ፤ እንዲሁም የስራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ስልጣን የፌደራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ እንዲገመግሙ፣ ገምግመው የይሁንታ ፈቃድ ለሰጧቸው እንዲከታተሉ ውክልና ለሰጣቸው መ/ቤቶች ከውክልናው ጋር የፕሮጀክቶችን ዝርዝርና የጥናት ቅጅያቸውን ባለማስተላለፉ ባለፕሮጀክቶቹ በሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት መስራታቸውን ባለስልጣኑም ሆነ ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ የማረጋገጥና የመቆጣጠር ስራ ያልሰሩ መሆኑ።

113. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ግምገሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ የማያሳውቅ መሆኑን፤እንዲሁም በኦዲቱ ከታዩት 46 ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 40ዎቹ የአካባቢ ኦዲት ስለማድረጋቸው አረጋግጦ የማያውቅ መሆኑ፤

114. ባለስልጣን መ/ቤቱ ነባር ፋብሪካዎች የሚያስከትሉት ሊወገድ የማይችል አሉታዊ ተፅእኖ ሲኖር በደንብ በተቀመጠው የ5 አመት ግዜ ገደብ ውስጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያስወግድ የሚችል አስተዳደራዊ እርምጃ አለመውሰዱ፤

115. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የሰጣቸው ኢንዱስትሪዎችን በአካባቢ አያያዝ ና አጠባበቅ ዙሪያ ሙሉ በሙሉ ክትትል እና ቁጥጥር አለማድረጉ፤

እንዲሁም ለክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እንዲከታተሉ እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ በውክልና አለማስተላለፉ፤

116. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸውን በካይ ኬሚካሎችን አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት የሚወገዱበትን ሁኔታ ያላመቻቸ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

117. ስለሆነም ከላይ የተገለፁትን በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ግድፈቶች ለማስወገድ ወይም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብለው የታሰቡ የማሻሻያ ሃሳቦችን በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

118. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በስትራቴጂክ ዕቅዱ ያቀዳቸውን ተግባራት በዓመታዊ ዕቅድ በማካተት ተግባራዊ ሊያደርግና በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች ውስጥ የሚገለፁ ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚያስችል በተሟላ መልኩ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

119. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሀገሪቱ የሚገኙ ደኖች፣የብዝሀ ህይወት፣ የአየር ሁኔታ፣ ወንዞችና ሐይቆች ከደረቅ እና ከፍሳሽ ቆሻሻ የሚደርስባቸውን ብክለት በተመለከተ ያሉበትን ደረጃ፣ በፊት የነበሩነትን፣ የተጎዱትን/የተሻሻሉበትን ሁኔታ ወደፊት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችን እና መፍትሄዎች በማካተት አከባቢን በሚመለከት ፖሊሲን ለማውጣት እንዲያስችለው በየወቅቱ የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ አዘጋጅቶ በአካባቢ ምክር ቤት ሊያፀድቅ እና ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ ሊያደርግ እንዲሁም በሀገሪቷ ውስጥ ያሉትን በካይ ነገሮች ማለትም ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች ብዛት ፣ምንጫቸውን ከየት ሀገር እደመጡ፣መቼ እደተመረቱ፣ምን ያህል ጊዜ እደሚቆዩ በተጨማሪም ወዴት ሀገር ተዘዋውረው እደሚወገዱ በዝርዝር የሚገልፅ ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡

120. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ኬሚካሎችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ ሊከተሉት የሚገባ ፖሊሲና ህግ(አዋጅ፣ ደንብ መመሪያ እና ደረጃ) ሊያዘጋጅና በስራ ላይ መዋላቸውን ሊያረጋግጥ እንዲሁም ባለስልጣኑ በአካባቢ ዙሪያ ያዘጋጃቸውንና የተፈቀዱትን የአካባቢ ፖሊሲ፣ህጎችና ደረጃዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

121. የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችላቸው እንዲሁም እንደክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ መመሪያዎችን ለማስተካከል እና ኢንዲስትሪዎች ስለ አካባቢ አጠባበቅ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እንዲያስችል እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱት ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚረዳ የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ህጎች፣አዋጆችና ደንቦች ተፈፃሚ እንዲሆኑ የተለያዩ መመሪያዎች እና ደረጃዎችን አውጥቶ በማፀደቅ ለዘርፍ መ/ቤቶች እና ለክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች በመላክ ክልሎችም በስራቸው ላሉት ኢንዱስትሪዎች በማስተላለፍ መመሪያዎቹና ደረጃዎቹ በስራ ላይ መዋላቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

122. በሀገሪቷ ውስጥ የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት ፣ ለአረም እና ለነፍሳት ማጥፊያ ተብለው በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ ሀገር የሚገቡ ኬሚካሎችን አያያዝ፣አጠቃቀም እና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያ በማዘጋጀት ለኢንዱስትሪዎች በመላክ በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ማድረግ አለበት፡፡

123. በክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣናት የክህሎት ክፍተት እንዳይኖር፣የክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች ኢንዱስትሪዎችን ለመቆጣጠርና ለመከታተል እንዲያስችላቸው እንዲሁም የአካባቢ አያያዝንና አጠባበቅን በሚመለከት ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲረዳቸው የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም የዘርፍ መ/ቤቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያከናውኑ እና በውክልና የተሰጣቸውን ኃላፊነቶች ለመወጣት እንዲያስችላቸው ተከታታይነት ያለው የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና መስጠት አለበት ፡፡

124. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች እና ከዘርፍ መ/ቤቶች ጋር የአካባቢ አጠባበቅን በተመለከተ መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት ሊሰራ እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ በአካባቢ ዙሪያ የተከናወኑና ያልተከናወኑ ተግባራትን ለይቶ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት እንዲያስችለው ከክልሎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በአካባቢ ዙሪያ ሪፖርቶችን በወቅቱ ለመለዋወጥ የሚረዳ የመግባቢያ ሰነድ (memorandum of understanding) ሊኖረው ይገባል፡፡

125. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሀገሪቱ ያሉት ኢንዱስትሪዎች መረጃ በዓይነት፣ በብዛት፣ በአካባቢ ለማወቅ የሚያስችል፣ ወቅታዊ የሆኑና በአካባቢ ላይ የወጡ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን እና መመሪያዎችን በአካባቢ ጥበቃ ሁኔታዎች ላይ ለመገንዘብ የሚረዳ የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣አሰባሰብን፣አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

126. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በየክልሉ ያሉት ኢንዱስትሪዎች ያሉበትን ደረጃ፣የሚፈልጉትን ድጋፍ ለማወቅ የሚያስችል እና ጥቅል የሆነ ሀገራዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል በአግባቡ ለማቅረብ የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት በመዘርጋት የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን እንዲሁም የዘርፍ መ/ቤቶች /የሚኒስቴር መ/ቤቶች/ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እድያሳውቁት እና እንዲልኩለት ሊያደርግ በተሰጣቸው ውክልና ላይ በተቀመጡት ዝርዝር ተግባራት መሰረት መስራታቸውን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

127. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አሃድን አስፈላጊነት ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች አውቀው በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ትኩረት ሰጥተው ለመስራት እንዲያስችላቸው የአካባቢ ነክ ጉዳዩችን የሚከታተል ክፍል እንዲያቋቁሙ ማድረግ አለበት፡፡

128. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ ገምግሞ የይሁንታ ፈቃድ ለሰጣቸው በዘገባው በተዘረዘሩት ግዴታዎች መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

129. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 295/95 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 5 መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ ገምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ማሳወቅ ይኖርበታ፡፡

130. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት በአግባቡ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

131. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በፌዴራል ደረጃ ፍቃድ ለተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ አያያዝና አጠባበቅ ዙሪያ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ወይም ክልሎች ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዲያስችላቸው በውክልናው ላይ እንዲስቱሪዎችን ከነዝርዝራቸው ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

132. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጊዜ ያለፈባቸውን በካይ ኬሚካሎችን በሰው፣ በእንስሳት እዲሁም በእፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአደገኛ ኬሚካል አወጋገድ መመሪያ በማዘጋጀት በሀገሪቱ ያሉትን በካይ ኬሚካሎች መጠንና ዓይነት ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡

133. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በደንብ ቁጥር 159/2001 በተቀመጠው የ5 አመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከነባር ፋብሪካዎች ሳይታከሙ የሚለቀቁ ቆሻሻ ፍሳሾች በአካባቢው፣ በወንዞችና በሀይቆች ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት እና እፅዋት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ እና የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሀን እንዳይበክሉ በአካባቢው ላይ ሊወገድ የማይቻል አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትሉትን ፋብሪካዎች በመለየት አሉታዊ ተፅኖውን ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የባለሥልጣኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች፣ በኦዲቱ መረጃ የሰበሰብንባቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የክልል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣናት ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| | የኦዲት ጭብጦች<br>(Audit Issues) | የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች<br>(Evaluative criteria) |
|---|---|---|
| 1. | በባለስልጣኑ በተዘገቡ ዘገባዎች መሰረት የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓትን ለማስፈን የወጡ የአካባቢ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ደረጃዎች እና መመሪያዎች ተፈፃሚነትን እና ውጤታማነትን ለመገምገም ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | 1. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት በተፈቀደለት መዋቅር መሰረት የሰው ኃይል ሊያሟላ ይገባል፡፡ |
| | | 2. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስትራቴጂክ ዕቅድ ያቀደውን ተግባራት በዓመታዊ ዕቅድ ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 3. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በየዓመቱ በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት መሰረት ለሚታዩ ክፍተቶች እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | | 4. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀገሪቱን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግስትና ለህዝብ ይፋ ሊያደር ግይገባል፡፡ |
| | | 5. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደገኛ ነገሮችን /ኬሚካሎችን/ ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን በተመለከተ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲና ህግ /አዋጅና ደንብ / ሊያዘጋጅና ሌሎች የአካባቢ ህጎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | | 6. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ለመመርመርና ውሳኔ ለመውሰድ የሚያስችል የአካባቢ ህግ፣ ደረጃ እና መመሪያ አዘጋጅቶ ለዘርፍ መ/ቤቶች ሊልክ ይገባል፡፡ |
| | | 7. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎችን ሊያዘጋጂ እና ለክልል አካባቢ ጥበቃ ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች/ ሊልክ እንዲሁም ክልሎችም ለኢንዱስትሪዎች በመላክ በስራ ላይ ማዋላቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | | 8. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን በሚመለከት ለክልሎች ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 9. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ምርመራና ውሳኔ አወሳሰድ ላይ ለዘርፍ መ/ቤቶች የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፡፡ |
| | | 10. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአካባቢ እንክብካቤ እና አያያዝ ዙሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች፣ድርጅቶችና ግለሰቦችን በማወዳር የማበረታቻ ዘዴዎችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | | 11. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የሀገሪቱን የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚያመለክት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት ዓመቱ ሊያወጣ ይገባል |
| | | 12. የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ /ማምከንን/ አሰመልክቶ መመሪያ በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | | 13. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ እንክብካቤን በተመለከተ ለህብረተሰቡ መደበኛ ያልሆኑ የአከባቢ ትምህርት በመስጠትና የተለያዩ ዘዴዎችን (ብሮሸር፣ ሬድዮ፣ ቲቪ፣ ካላንደር ወዘተ…) በመጠቀም ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይገባል፡፡ |
| 2. | ባለስልጣኑ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የሆነ | 14. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የመወያያና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | | 15. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሪፖርት አቀራረብና አደራረግን በተመለከተ ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የመግባቢያ ሰነድ (memorandum of understanding) ሊኖረው |

| | | |
|---|---|---|
| | የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ እንዲሁም ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | ይገባል፡፡ |
| | | 16. የፌዴራል አከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአከባቢ ጉዳዮችን በመደበኛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡ |
| | | 17. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ መረጃ ልውውጥን፣ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | | 18. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአገልግሎት ሰጪ እና የማምረቻ ተቋማት ክትትልን በተመለከተ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እድያሳውቁት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 19. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ሰነድ ቅጂና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የዘርፍ መ/ቤቶች /የሚኒስቴር መ/ቤቶች/ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ እዲልኩለት ሊያደርግ እና በተሰጣቸው ውክልና መሰረት ስለመስራታቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| 3. | የአከባቢ አሃድ /Enivronmental unit/ በዘርፍ መ/ቤቶች መቋቋሙን እንዲሁም በወጡ የአከባቢ ስርዓት አተገባበር ላይ ለኢንዱስትሪዎችና ለባለድርሻ አካላት የሚደረገው ክትትልና ግምገማ ብቃት ባለው መልኩ መደረጉን መገምገም፡ | 20. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ አሃድን/ የአካባቢ ነክ ጉዳዩችን የሚከታተል ክፍል/ ሁሉም የዘርፍ መ/ቤቶች እና ኢንዱስትሪዎች እንዲያቋቁሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ |
| | | 21. ባለስልጣን መ/ቤቱ የፀደቁ የአካባቢ ሕጎች እና ፖሊሲዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | | 22. ባለስልጣን መ/ቤቱ የስራ ፈቃድ የመስጠት፣ የመተግበር ወይም ክትትል የማድረግ ስልጣን የፌደራል መንግስት የሆነባቸው ወይም ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ሊገመግም ገምግሞ የይሁንታ ፈቃድ ለሰጣቸው ሊከታተል እንዲሁም በሰነዱ በተቀመጡ ግዴታዎች መሰረት ስለመስራታቸው ሊያረጋግጥና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | | 23. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ሰነድ ግምግሞ ፈቃድ ለመስጠት ውክልና ለተሰጣቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የግምገማውን ውሳኔ በወቅቱ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ |
| | | 24. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | | 25. የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የሰጣቸው ኢንዱስትሪዎችን በአከባቢ አያያዝ ና አጠባበቅ ዙሪያ ሊከታተልና ቁጥጥር ሊያደርግ ወይም ክልሎች እንዲከታተሉ እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ በውክልና ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡ |
| | | 26. በባለስልጣን መ/ቤቱ ጊዜ ያለፈባቸውን በካይ ኬሚካሎችን በሰው፣ በእንስሳት እዲሁም በእፅዋት ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት የሚወገዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ |
| | | 27. የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፋብሪካው እንቅስቃሴ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ ሊወገድ የማይቻል ከሆነ ይህንን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ |